
# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
# ሪፐብሊክ መንግሥት
# የትምህርት ሚኒስቴር



# ሀገር አቀፍ የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ



ትምህርት ሚኒስቴር
የካቲት/2000
አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# ትምህርት ሚኒስቴር

ማውጫ ገጽ

መግቢያ ........................................................................1

2. የጎልማሶች ትምህርት ያለበት ሁኔታ ..............................4
2.1 የጎልማሶች ትምህርት አቅርቦት በሚፈለገው መጠን አለመስፋፋት .........................................................5
2.2 ፍትሐዊ የሆነ የጎልማሶች ትምህርት ሥርጭት አለመኖር 6
2.3 የጎልማሶች ትምህርት ተገቢነትና ጥራት ዝቅተኛ መሆን፣.8
2.3.1 ከተገቢነት አንፃር ሲታይ ..........................................8
2.3.2 ከጥራት አንፃር .........................................................9
2.4 የጎልማሶች ትምህርት አጠናክሮ በአግባቡ የሚመራ አደረጃጀት አለመኖር ..........................................10
2.5 በጎልማሶች ትምህርት ተመጣጣኝ የሆነ የሀብት ምደባ አለመኖር ..............................................................12

3. የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ ዓላማዎችና ግቦች ........14
3.1 አጠቃላይ ዓላማ .......................................................14
3.2. ስትራቴጂካዊ ግቦች ..................................................14
3.2.1 የስትራቴጂክ ግቦችን ማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች ..............14

4. የምንከተላቸው ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች .......................15
4.1 የጎልማሶች ትምህርትን በማስፋፋት ሽፋኑን ማሳደግ.......15
4.1.1 በጎልማሶች ትምህርት አስፈላጊነት ላይ የግንዛቤ ሥራ መስራት ...............................................................15

4.1.2. ለተደራጀ አሠራር አስፈላጊውን በጀትና የሰው ሀይል መመደብ ....................17
4.2. ጥራትና ተገቢነት ያለው የጎልማሶች ትምህርት ሥርዓት መዘርጋት ....................18
4.2.1 ሥርዓተ ትምህርት ....................19
4.2.2. የጉልማሶች ትምህርት አመቻቾችን፣ ሱፐርቫይዘሮችንና ሌሎች ባለሙያዎችን የማስፈፀም አቅም መገንባት..........21
4.2.3 የትምህርት መሣሪያዎችና ቁሳቁሶችን በማሟላት ምቹና ዘላቂነት ያለው የመማሪያ አካባቢ መፍጠር ....................23
4.2.4. ለውጤታማ የጎልማሶች ትምህርት የትምህርቱን አሰጣጥ ስልቶችንና ቴክኒኮችን ማሻሻል ....................24
4.3. የጎልማሶች ትምህርትን ሽፋን በፍትሃዊነት ማሳደግ፣......25
4.4. የጎልማሶች ትምህርት በተከታታይ የሚሰጥበት ተቋማዊ ሥርዓት መዘርጋትና አቅም መፍጠር ....................26
4.4.1 የጎልማሶች ትምህርት አመራርና አደረጃጀት ....................26
4.4.2. ዘላቂና ውጤታማ የግንኙነት መረብ መዘርጋትና አጋርነትን መፍጠር ....................27
4 .4.3. ውጤታማ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት........28

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች በመፈቃቀድ በጋራ የሚኖሩባት አገር ስትሆን የሕዝብ ብዛቱ 1999 ዓ.ም. 75 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ አገሪቷ በሕዝብ ብዛት ከአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ስትገኝ 80% የሚሆነው ሕዝቧ በገጠሩ የአገሪቱ ክፍል ነዋሪ ነው፡፡ ዩኔስኮ በእ.ኤ.አ. በ2006 ባሳተመው Global EFA monitoring Report ዕድሜው 15 እና ከዚያ በላይ ከሆነው ሕዝብ 58.5 % ማንበብና መጻፍ የማይችል/ማይም/ ነው፡፡

ትምህርት ለልማት ቁልፍ መሣሪያ ከመሆኑም ባሻገር ማንኛውም ሰው ልጅ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖትና በኢኮኖሚ ደረጃ ልዩነት ሳይደረግበት በተለይ መሠረታዊ ትምህርት ሊያገኘው የሚገባ መብቱ ነው። ይህንን የዜጎችን የመማር መብት ለማስከበርና ትምህርት የሚያስገኛቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎችን እውን ለማድረግ በአገራችን አዲስ ፌደራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት ከተዘረጋ ወዲህ በተዘጋጀው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት አድርገው በተከታታይ በወጡት የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች ሕብረተሰቡን የትምህርት ተጠቃሚ ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነው፡፡

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ዋነኛ ዓላማ በአገሪቱ ውስጥ በሚካሄዱ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በብቃት መሳተፍ የሚችል በተለያዩ ደረጃዎች የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት ነው። ይህንን ዓላማ ለማሳካት የትምህርት ሥርዓቱን መሠረታዊ ጉድለቶች ማለትም የትምህርት አቅርቦትን ለማስፋፋት፣ የሥርጭቱን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ፣ ጥራቱን ለመጠበቅና ተገቢነቱን ለማረጋገጥ ደረጃ በደረጃ ያላሰለሰ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል። ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ በተከታታይ በወጡና በሥራ ላይ በዋሉ የትምህርት ልማት ዘርፍ በፕሮግራሞች አማካኝነት ባለፉት ዓመታት የአገሪቱን የትምህርት አቅርቦት ለማስፋፋት በተደረገው ጥረት የትምህርት ተሳትፎን በየደረጃው ከነበረበት ማሳደግ ተችሏል።

ይሁን እንጂ የጎልማሶች ትምህርት በሚገባ ካለመስፋፋቱ ባሻገር በማምረት ሥራ ላይ ቀጥተኛ ተሣታፊ ለሆነው የሕብረተሰብ ክፍል የሚሰጠው ትምህርትና ሥልጠና ከጎልማሳው ዕለታዊ ኑሮ ጋር ያልተዛመደ፣ በችግር ፈቺነት ላይ የተመሠረተ ብቃት የሚያላብስ አለመሆኑና በተለያዩ የልማት መስሪያ ቤቶች የሚደረጉ ጥረቶችን አቀናጅቶ መንቀሳቀስ አለመቻሉ የትምህርት ዘርፉ አንዱ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም እነዚህን የጎልማሶች ትምህርት ችግሮች ለመፍታት እንዲቻል ህብረተሰቡ ለልማት በሚደረገው ጥረት ውስጥ በስፋት በማሳተፍ የተለያዩ የሕይወት ክህሎት ዘርፎችን ያካተተ ተግባር - ተኮር

የጎልማሶች መሠረተ ትምህርት ፕሮግራሞች እንደሚስፋፉ በሦስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ተገልጿል ። ይህም አገሪቱ ድህነትን ለማስወገድና ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፓኬጆችን (የግብርናና የገጠር፣ የኢንዱስትሪ፣ የጤና የወጣቶች ሴቶች ወዘተ) ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገው ርብርብ የጎልማሶች ትምህርት ሊያበረክት የሚችለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ግምት መሠጠቱን የሚያመላክት ነው።

በመሆኑም የጎልማሶች ትምህርትን ማስፋፋትና ማጠናከር የሕብረተሰቡን ምርታማነት ከማሳደጉም ባሻገር ጤንነቱ የተጠበቀ፣ መረጃን በቀላሉ ማግኘትና መጠቀም የሚችል ህብረተሰብ ለመገንባት እንዲያስችል የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የጎልማሶች ትምህርት ጎልማሳውን እውቀትና ክህሎት ለማስጨበጥና ወደፊት በስፋት የሚያካሂደውን ፕሮግራም ሙያ-ተኮር የጎልማሶች ትምህርት Functional Adult Literacy (FAL) ለማድረግ ሲሆን፡-

እንደ ግብርና፣ ጤና፣ የስነ-ዜጋ፣ ባህላዊ ትምህርትና... ወዘተ የመሳሰሉትንና ለሌላውም የሕይወት ገጽታ ጠቃሚ የሆኑ እውቀትና ክህሎቶችን ለመካን መጻፍና ማንበብን መቅሰምና

መጠቀም ነው፡፡ ይህም በአሁኑ ጊዜ በብዙ ቦታዎች በመተግበር ላይ ይገኛል።

ስለዚህ በኢትዮጵያ የሚያካሂደውን ልማትና ሁለንተናዊ እድገት ለማፋጠን ለጎልማሶችና የመደበኛ ትምህርት እድል ላላገኙ ወጣቶች ተግባር-ተኮር የጎልማሶች መሠረተ ትምህርት ማካሄድ እጅግ ጠቃሚ ነው። በመሆኑም የሚመለከታቸው አካላት ንቁ ተሣትፎ ያደረጉበት የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ የጎልማሶች ትምህርት ያለበትን ሁኔታና ተገቢነት ያለው የጎልማሶች ትምህርት በስፋትና በጥራት ለማካሄድ የምንከተላቸው ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችና እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ የጎልማሶች ትምህርት አመራር አደረጃጀት ተካቷል።

## 2. የጎልማሶች ትምህርት ያለበት ሁኔታ

የጎልማሶች ትምህርት ዕድሜው 15 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል ከመሠረታዊ የንባብ፣ የጽሕፈት፣ የስሌትና ክህሎት ሥልጠና ጀምሮ እውቀቱንና ችሎታውን ለማሳደግ በተደራጀ ሁኔታ የሚሰጥ የትምህርት ሂደት ነው፡፡

ሀገራችን ከምትገኝበት ዝቅተኛ የልማት ደረጃ ወደ ተፋጠነ ዘላቂ ልማት ለማሸጋገር የሰብአዊ ሀብት ልማት ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል፡፡ መሬትንና ሌሎች ቁሳዊ ሀብቶችን በአግባቡ ይዞና ተጠቅሞ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በምርት ሥራ ላይ የተሰማራውን ሰብአዊ ሀይል (ወጣቱንና ጎልማሳውን) አቅም በትምህርትና ሥልጠና መገንባት አስፈላጊነቱ በተለያዩ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ የጎልማሶች ትምህርት ከዘመን ዘመን ሲንከባለሉ የመጡ የተለያዩ ችግሮች ይታዩበታል፡፡ እነዚህ በጎልማሶች ትምህርት የሚታዩና ሊወገዱ የሚገባቸው ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 2.1 የጎልማሶች ትምህርት አቅርቦት በሚፈለገው መጠን አለመስፋፋት

በአንድ ሀገር ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፍትሐዊ የገቢ ክፍፍልና የተመጣጠነ ንቁ የፖለቲካ ተሣትፎ እንዲሰፍን የትምህርት አገልግሎትና አቅርቦትን ለህብረተሰቡ ማዳረስ አስፈላጊ ነው፡፡ መንግሥት ትምህርትን በተለይ መሠረታዊ ትምህርትን ለዜጎች ለማዳረስ በወሰዳቸው እርምጃዎች በመደበኛ ትምህርት ተሳትፎ ሽፋን አንፃር አበረታች ውጤቶች በየደረጃው ተመዝግበዋል፡፡ መሠረታዊ ትምህርትን ለጎልማሶች ለማዳረስ በተደረገ ውስን ጥረት የማይምነትን ምጣኔ (illiteracy rate) ወደ 58.5% ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

በአለፉት ዓመታት በክልሎች የተካሄዱ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞች ተከታታይነትና ዘላቂነት የጎደላቸው ከመሆኑም ባሻገር በጥቂት ክልሎች በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ የሚካሄዱ ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ አብዛኛው በእቅድና ፕሮግራም የማይመሩና ተከታታይነት የጎደላቸው ናቸው። በሀገር ልማት ቀጥተኛ ተዋናይ ስሆነው የሕብረተሰብ ክፍል/ለጎልማሳው/ የትምህርት አቅርቦትን ለማስፋፋት የተደረገው ጥረት ውስን በመሆኑ የማይምነትን ምጣኔ (illiteracy rate) በሚፈለገው መጠን መቀነስ አልተቻለም። ከዚህም በተጨማሪ የጎልማሶች ትምህርት ያለበትን ሁኔታ የሚገልፅ የተሟላ መረጃ በሀገር አቀፍ ደረጃ አለመኖሩ ሌላው የሚጠቀስ ችግር ነው።

ጎልማሳው እውቀቱንና ክህሎቱን አዳብሮ በሀገር ልማት በብቃት እንዲሣተፍ ከመንግሥት የልማት ስትራቴጂዎች በተለይ ከግብርናና ገጠር ልማት፣ ከጤና እንዲሁም ከሴቶችና ወጣቶች የልማት ፓኬጆች ወዘተ... ጋር የሚጣጣም፣ ለእነኝህ የልማት ሥራዎች መፋጠንና በዘላቂነት ለመጠቀም በመሣሪያነት የሚያገለግል የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ማስፋፋት ተገቢ ነው።

## 2.2 ፍትሐዊ የሆነ የጎልማሶች ትምህርት ሥርጭት አለመኖር

ትምህርት ከልማት መሣሪያነቱ ባለፈ ማንኛውም የሰው ልጅ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖትና በኢኮኖሚ ደረጃ ልዩነት ሳይደረግበት

ሊያገኙት የሚገባው መብት ነው። ይህንን የዜጎችን የመማር መብት ለማስከበርና ትምህርት ለሕብረተሰቡ የሚያስገኘውን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እውን ለማድረግ በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ትምህርትን በተለይ መሠረታዊ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ለማዳረስና ሥርጭቱን ፍትሐዊ ለማድረግ ጥረቶች ተደርገዋል።

የትምህርት ሥርጭት ፍትሐዊነት ከሚገለጹባቸው መስፈርቶች መካከል በከተማና በገጠር፣ በወንድና በሴት እንዲሁም በክልሎች መካከል ያለውን የትምህርት ሥርጭት ማመጣጠን ነው። በክልሎች እንዲሁም በገጠርና በከተሞች የተመጣጠነ እድገት መኖር የዜጎችን በራስ የመተማመን ስሜት ከማሳደጉም በተጨማሪ ለምናካሂደው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፅኑ መሠረት ነው። የሀገራችንን ልማት ለማፋጠን በሚደረገው ጥረት ግማሽ ያህሉን የልማት አቅም ወደጎን በመተው እድገት ማምጣት አይቻልም። ሴቶችን ማስተማር ቤተሰብንና ሕብረተሰብን ማስተማር በመሆኑ ለእድገትና ልማት ጽኑ መሠረት ናቸው።

ይሁን እንጂ ባለፉት ዓመታት የጎልማሶች ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ በጥቂት ክልሎች ከሚደረጉ ውስን ጥረቶች በስተቀር በአብዛኛዎቹ ክልሎች ፕሮግራሙ ጭራሹን አልተጀመረም። በተካሄደባቸው ክልሎችም ቢሆን ካለው የተዛባ ልማዳዊ አመለካከት፣ ከትምህርት ፕሮግራሙ ተስማሚ አለመሆንና በቤት

ውስጥ ካለባቸው የሥራ ጫና የተነሳ የሴቶች ተሣትፎ እጅግ አነስተኛ ነው። በተጨማሪም በአብዛኞቹ ቦታዎች ጎልማሶች የእድሉ ተጠቃሚ አልነበሩም። ይህ የተሣትፎ ልዩነት ሊጠብ ብሎም የማይምነት ደረጃ ሊቀንስ ይገባል። ጎልማሶች ለትምህርት እድል እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑና ለድህነት ቅነሳና ለዘላቂ ልማት መረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በዘርፉ ጠንክረን መሥራት ይጠበቅብናል።

## 2.3 የጎልማሶች ትምህርት ተገቢነትና ጥራት ዘቅተኛ መሆን፣

### 2.3.1 ከተገቢነት አንፃር ሲታይ

ከጎልማሶች ትምህርት ሥርጭት፣ ማስፋፋትና ተሣትፎ ጋር በተያያዘ የሚሰጠው ትምህርት ጥራቱን የጠበቀና ተገቢነት ያለው እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው። በመሠረቱ ጎልማሳው ለመማር የሚነሳሳው ትምህርቱ በፍላጎቱና በችግሩ ላይ የተመሰረተ ከእለት ተግባሩ ጋር የተገናዘበ፣ ወዲያውኑ ሲተገብረው የሚችል ችግር ፈቺና ተገቢነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ነው።

ተግባር-ተኮር መሠረተ ትምህርት አርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩን፣ ሴቶችና ወጣቶች በተለያዩ የልማት ፓኬጆች ያገኙትን እውቀትና ክህሎት በዘላቂነት ለመጠቀም ያስችላቸዋል። እንዲሁም ለመረጃ በሚኖራቸው ቅርበት ተጨማሪና አዳዲስ ክህሎት የመፈለግና

ያገኙትን አሻሽሎ በመጠቀም ኑሯቸውን ያሻሽላሉ ምርታማነትን ያሣድጋሉ፡፡

ይሁን እንጂ በአለፉት ዓመታት በተካሄዱ ውስን የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞች የሚሰጠው ትምህርት ከጎልማሶች እለታዊ ኑሮና ክልማት ጋር ያልተያያዙ ንባብ፣ ጽህፈትና ስሌትን ለማስቻል ብቻ የተካሄዱ በመሆናቸው በተሣታፊ ኑሮ ዘንድ የሚፈለገውን ያህል ለውጥ ማምጣት አልቻሉም፡፡

## 2.3.2 ከጥራት አንፃር

ለትምህርት ጥራት መሠረታዊ ግብአት ከሆኑት አንዱ የጎልማሶች ትምህርት አመቻች (መምህራን) ብቃትና በተፈላጊው መጠን መገኘት ነው፡፡ ጎልማሶች ካላቸው ግለሰባዊ ማንነት፣ በማሕበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ቦታና ኃላፊነት በላይ የብዙ ተሞክሮዎች ባለቤት በመሆናቸው እነርሱን ማስተማር የተለየ ዘዴን ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት ዓመታት የጎልማሶች ትምህርት አመቻቾች ምልመላ ወጥነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር የተደራጀ ተቋማዊ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ሳይዘረጋ ቆይቷል፡፡

ከትምህርት ጥራት ጋር የሚያያዘው ሌላው ጉዳይ የሥርዓተ ትም/ዝግጅትና የመጽሐፍት ሕትመት በሚገባ አለመኖር፣ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍትና ሌሎች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በበቂ ሁኔታ አለመሟላት ነው፡፡ በዚህ በኩል የመማሪያ መጽሐፍትን በማዘጋጀት ጥረት የተደረገ ቢሆንም

የትምህርት ፕሮግራሙን በቀጣይነት ካለማካሄድ የተነሳ በተጠቃሚው ፍላጎት ላይ የተመሰረቱና ተገቢነት ያላቸው መጽሐፍት አዘጋጅቶ ለተጠቃሚ ጎልማሶች የማሠራጨት ሁኔታ ብዙም ያልተሄደበት ነው። በተጨማሪም የጎልማሶችን ትምህርት በዘመናዊ የመገናኛ መሣሪያዎች (በሬዲዮ በቲቪ ወዘተ) የማስተማር ዘዴዎች አልተደገፉም ነበር።

በመሆኑም ጥራትና ተገቢነት (የተለያዩ የግብርና የገጠር፣ የጤና፣ የሴቶችና የወጣቶች ፕሮግራሞችና ፓኬጆች ጋር የተጣጣመ) ያለው ትምህርት ለጎልማሶች ለመስጠት አመቺ መምህራንን በብቃትና በተፈላጊ መጠን ለማሰልጠን የተደራጀ ቀጣዊ የሥልጠና ሥርዓት መዘርጋት፣ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍትን በጥራት ማዘጋጀትና ለተጠቃሚው በማዳረስ እንደ ሬዲዮ፣ ICT ወዘተ የመሳሰሉትን በመጠቀም ለጎልማሳው አስታዊ ኑሮ ጠቃሚነትና ተገቢነት ያለው፣ በልማት ፓኬጆች ላይ የተመሠረተ ተግባር-ተኮር የመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም በስፋት ዘርግቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል።

## 2.4 የጎልማሶች ትምህርት አጠናክሮ በአግባቡ የሚመራ አደረጃጀት አለመኖር

የትምህርት ሥራ ውጤታማ የሚሆነው ሁሉም የሕብረተሰብ አካላት የሚጠበቅባቸውን ድርሻ በጋራ ለመወጣት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ሲፈጠር ነው። በአገራችን የተዘረጋውን ያልተማከለ

የአስተዳደር ሥርዓት ተከትሎ የትምህርት አመራርም ሆነ ሌላው የልማት ዘርፍ ወደ ወረዳ እንዲወርድ ተደርጓል፡፡ በአለፉት ዓመታት የተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ወጣቶችን፣ ሴቶችንና ጎልማሶችን በተለያዩ የኤክስቴንሽንና የልማት ፓኬጆች በማስተማርና በማሰልጠን ውጤት በማስመዝገብ ላይ መሆናቸው ይታመናል፡፡ በትምህርት ዘርፉም እንዲሁ በክልሎች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተደረጉ ጥረቶችና ተሞክሮዎች እንዳሉ ጠቀሜ ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ በተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የሚደረጉ ጥረቶች የመጨረሻው ግብ አምራቹን የሕብረተሰብ ክፍል አቅም በመገንባት ኑሮውን እንዲያሻሽልና ለልማት በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት በብቃት እንዲሣተፍ ማስቻል ነው፡፡ የጎልማሶች ትምህርት የልማት ስትራቴጂዎችንና ፓኬጆች በተጠቃሚው ዘንድ ስርፀት እንዲያገኙ በልማት መሣሪያነት ሚናውን ይጫወታል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ጥረቶች አቀናጅቶ የሚመራና የሚያስተባብር ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው አደረጃጀት ባለመኖሩና በየደረጃው ያሉት የትምህርት አመራሮች ትኩረት ያለመስጠትና የግንዛቤ ማነስ ችግሮች ያሉንን ውስን ሀብት በጋራና በአግባቡ ለመጠቀም አላስቻለም፡፡

በመሆኑም የጎልማሶች ትምህርት በአንድ መስሪያ ቤት ብቻ የሚከናወን ፕሮግራም ሳይሆን የተለያዩ የልማት መስሪያ ቤቶችን የልማት አጋሮችን የተቀናጀ ጥረት የሚሻ በመሆኑ ለዚህ ኃላፊነትና

ተጠያቂነት ያለው ተስማሚ የጎልማሶች ትምህርት አመራር አደረጃጀት መኖር አስፈላጊ ነው።

## 2.5 በጎልማሶች ትምህርት ተመጣጣኝ የሆነ የሀብት ምደባ አለመኖር

ማንኛውም የትምህርት ሥርዓት በተገቢው ሁኔታ ለማካሄድና ከታለመለት ግብ ለማድረስ መሠረታዊ፣ ሰብአዊ፣ ቁሳዊና የፋይናንስ ግብአቶች በተሟላ መልኩ መገኘት አስፈላጊ ነው። መንግሥት በየዓመቱ ለትምህርት ሴክተሩ የሚመድበው በጀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ለትምህርት ዘርፉ ከተመደበው ውስጥ የጎልማሶች ትምህርት ድርሻ እጅግ አነስተኛ ነው። ይህም ቢሆን ለሠራተኛ ደመወዝ የሚውል ነው። በየደረጃው ለዘርፉ የተመደበ የሰው ኃይልም እጅግ አነስተኛና ከሙያውም ጋር የተዛመደ ሥልጠና የሌለው ነው። በመሆኑም የጎልማሶች ትምህርትን በተቀናጀ መልኩ አጠናክሮ ለማካሄድ ከአደረጃጀቱ ጋር ተመጣጣኝ በጀትና የሰው ኃይል ሊመደብለት እንደሚገባ ይታመናል።

የስትራቴጂው አስፈላጊነት፡-

- ድህነትን ለማስወገድና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ለአምራቹ የሕብረተሰብ ክፍል በተለያዩ አካላት የተዘጋጁ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች የልማት ፖኬጆችንና ፕሮግራሞች

በትምህርት በመደገፍ ትምህርት በልማት መሣሪያነት ሚናውን በሚፈለገው መጠን እንዲጫወት ለማስቻል፣

- በክልሎች የሚካሄዱ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን ከተለያዩ የልማት መስሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት ተከታታይነትና ዘላቂነት ባለው መንገድ የተጠቃሚውን ፍላጐትና የልማት ፖኬጆችን መሰረት ባደረገ የትምህርት ፕሮግራም ለማካሄድ፣
- በአገር ልማት ቀጥተኛ ተዋናይ የሆነውን የሕብረተሰብ ክፍል ለማስተማር ወጥነትና ሁሉንአቀፍ ፕሮግራም በመዘርጋት የማይምነትን ምጣኔ /illiteracy rate/ በ50% በመቀነስ የትምህርት ለሁሉምና የምዕተ ዓመቱን ግቦች ለማሳካት፣
- አምራቹ የሕብረተሰብ ክፍል /ጎልማሳው/ እውቀቱና ክህሎቱን አዳብሮ በአገር ልማት ውስጥ በብቃት ለመሳተፍ የሚያግዝ ከመንግሥት የልማት ስትራቴጂዎች በተለይ፣ከግብርናና፣ከጤና፣ እንዲሁም ከሴቶችና ከወጣቶች የልማት ፖኬጆች ወዘተ ጋር የሚጣጣምና ለነዚህ የልማት ሥራዎች መሣለጥና ዘላቂነት በመሣሪያነት የሚያገለግል ተግባር- ተኮር የጎልማሶች ትምህርት እንዲኖር ለማስቻል፣

## 3. የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ ዓላማዎችና ግቦች

### 3.1 አጠቃላይ ዓላማ

በኢትዮጵያ የማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት ውስጥ በብቃት ለመሳተፍ የሚያስችል ጥራትና ተገቢነት ያላቸው የትምህርት ፕሮግራሞችን የማግኘት እድል ለወጣቶችና ጎልማሶች የሚከፍት የታቀደ፣ የተደራጀና የተቀናጀ የጎልማሶች ትምህርት ስርዓት መዘርጋት፣

### 3.2. ስትራቴጂካዊ ግቦች

1. የጎልማሶች ትምህርትን በማስፋፋት የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ባህል መገንባት፣
2. የጎልማሶች ትምህርትን በማስፋፋት የሕብረተሰቡን ማሕበራዊ ሕይወት መለወጥ፣
3. ጥራትና ተገቢነት ባለው የጎልማሶች ትምህርት ሥርዓት ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማት ማረጋገጥ፣

#### 3.2.1 የስትራቴጂክ ግቦችን ማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች

1. የጎልማሶች ትምህርትን ማስፋፋት፣
2. ጥራትና ተገቢነት ያለው የጎልማሶች ትምህርት ስርዓት መዘርጋት፣

3. የጎልማሶች ትምህርትን ሽፋን በፍትሐዊነት ማሳደግ፣
4. የጎልማሶች ትምህርት በተከታታይነት የሚሰጥበት ተቋማዊ ሥርዓትና አቅም መፍጠር፣

## 4. የምንከተላቸው ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች

### 4.1 የጎልማሶች ትምህርትን በማስፋፋት ሽፋኑን ማሳደግ

ሀገራችን በጀመረችው ድህነትን የመቀነስና ልማትን በዘላቂነት የማረጋገጥ ሂደት ግንባር ቀደም ተዋናይ የሆነውን አምራች የሕብረተሰብ ክፍል አቅም በትምህርትና ሥልጠና መገንባት የመንግሥት ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ነው። ስለሆነም የጎልማሶች ትምህርትን በስፋት ለማካሄድና ሽፋኑን ለማሳደግ በዘርፉ አስፈላጊነት ላይ የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ተቀዳሚ ተግባር ነው። በመሆኑም፦

#### 4.1.1 በጎልማሶች ትምህርት አስፈላጊነት ላይ የግንዛቤ ሥራ መስራት

- ጎልማሶች በተሰማሩበት ሙያ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ተግባር ተኮር የመሠረተ ትምህርት ፕሮግራሞች በስፋት ለማካሄድ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣በክልል መንግሥታት ቢሮዎችና በወረዳ ደረጃ እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መካከል ቀጣይነት ያለው

መግባባት በመፍጠር ለፕሮግራሙ መሳካት በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ፣

- የጎልማሶች ትምህርት ልማትን ለማፋጠን፣ ዲሞክራሲያዊ ባህልን ለመገንባትና ድህነትን ለማስወገድ ስለሚያበረክተው አስተዋጽኦ፣ የግለሰብንና የማህበረሰቡን ኑሮ ለማሻሻል ስለሚሠጠው ጠቀሜታ በየደረጃው ግንዛቤን ለማሳደግ በፌደራል፣በክልል በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የግንዛቤ ማስጨበጫና የአህዝቦት ሥራዎችን በማከናወን የጋራ መግባባት መፍጠር፣
- የተለያዩ የግንዛቤ ማዳበሪያና የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን (መገናኛ ብዙሀን፣ የሕትመት ውጤቶች፣ ኮንፈረንሶች፣ አውደጥናቶችንና ስብሰባዎችን ወዘተ) በመጠቀም የአስፈፃሚ አካላትን፣ የአጋሮችንና የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር፣
- ስለጎልማሶች ትምህርት ጠቀሜታ በቂ ግንዛቤ በየደረጃው በመፍጠር ህብረተሰቡ፣ የልማት መስሪያቤቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ሲቪል ማህበራት ፕሮግራሙን በማካሄድ የጎልማሶች ትምህርትን በገንዘብና ቁሳቁስ በመደገፍ ሽፋኑን ማሳደግ።

### 4.1.2. ለተደራጀ አሠራር አስፈላጊውን በጀትና የሰው ሀይል መመደብ

የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን በስፋት ለማካሄድና ሽፋኑን ለማሳደግ ከሥራው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሰው ሀይልና በጀት መመደብ፣ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም አስፈላጊው ነው። በዋናነት መዋዕለ ንዋይን በጎልማሶች ትምህርት ላይ ማዋል ከሌላው የሚለየው ውጤቱን በአጭር ጊዜ ማየት መቻሉ ነው በመሆኑም፡-

- ፌደራል መንግሥት፣ ክልሎችና ወረዳዎች ለዘርፉ የሚመድቡትን በጀት አቅም በፈቀደ መጠን በማሳደግና የበጀት ክፍተቱን ለመሸፈን ተጨማሪ ሀብት ከሌሎች ምንጮች በማፈላለግ ለጐልማሶች ትምህርት የሚውለውን መዋዕለ ንዋይ በየጊዜው ለማሳደግ የሚያስችሉ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ፤
- የሀብት (Resource) ማፈላለጊያና አጠቃቀም ሥልት ከአጋሮችና ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ማዘጋጀት፤ በተለይ የትምህርት ልማት አጋሮች ለዘርፉ የሚሠጡትን ድጋፍ ለማሳደግ በየደረጃው የሚደረገውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል፤
- ፕሮግራሙን በስፋት ለማካሄድና ሽፋኑን ለማሳደግ ከሚከናወነው ተግባርና ከሚጠይቀው ሀላፊነት አኳያ ተመጣጣኝ የሆነ የሰለጠነ የሰው ሀይል በየደረጃው ባለው የትምህርት ዘርፍ መመደብ.

- አስፈላጊ የሆኑ የጎልማሶች ትምህርት ተግባራትን በዘላቂነት ለማከናወን እንዲቻል በፌደራል፣ በክልል መንግሥታትና በጎልማሶች ትምህርት ማሠልጠኛ ተቋማት፣ ከአቅም ጋር የተገናዘበና ወጥነት ያለው የበጀት ፍሰት መኖሩን ማረጋገጥ፣
- ሕብረተሰቡን በመማሪያ ጣቢያዎች ግንባታና በትምህርት አመራር በማሳተፍ የተጠቃሚውን የባለቤትነት ስሜት ማረጋገጥ፣
- የተለያዩ ተቋማትን (የገበሬ ማሠልጠኛ ማዕከላት፣ የጤና ኬላዎችና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ቤቶችን) በመማሪያ ጣቢያነት በመገልገል ሀብትን በአግባቡ መጠቀም፣
- ማሕበረሰቡ በሚኖርባቸው አካባቢዎች (በቀበሌ) የመማሪያ ማእከላትን በዋናነት የገበሬ ማሠልጠኛ ማእከላትን፣ የጤና ኬላዎችንና የአማራጭ መሠረታዊ ትም/ቤቶችን የመማሪያ፣ የመዝናኛና የሀሳብ መለዋወጫ ማዕከላት በመሆን እንዲያገለግሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

## 4.2. ጥራትና ተገቢነት ያለው የጎልማሶች ትምህርት ሥርዓት መዘርጋት

የጎልማሶች ትምህርት ለግለሰብ፣ ለማህበረሰብ፣ ለሀገር ልማትና ሁለንተናዊ እድገት ትርጉም ያለው ፋይዳ ለማስገኘት በተጠቃሚው ማሕበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ስነ-ትምህርታዊ

ሁኔታዎች ላይ የተመሠረቱ ተገቢነት ያላቸውና ጥራታቸው የተጠበቀ የትምህርት ፕሮግራሞችን መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ከሥርዓተ-ትምህርት፣ ከመምህራን ሥልጠና፣ ከትምህርት መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች፣ ከትምህርት ድጋፍ አገልግሎት፣ ወዘተ... ጋር የተቆራኙ ስለሆነ እነዚህን ግብአቶች ማሟላት ጠቃሚ ነው።

## 4.2.1 ሥርዓተ ትምህርት

የጎልማሶች ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ እንቅስቃሴን፣ ሥራ ወዳድነትን፣ ፈጣሪነትን፣ አርቆ አስተዋይነትንና ዲሞክራሲያዊ ባህልን እንዲያዳብር ከማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት አኳያ አደረጃጀቱ ሊቃኝ ይገባዋል። ስርዓተ-ትምህርቱ የጎልማሳውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት አጎልብቶ አሠራሩንና ኑሮውን የሚያሻሽል ሊሆን ይገባዋል። በአጠቃላይ ጎልማሳው ልማት ተኮር አመለካከቱ የዳበረ፣ አካባቢውን ተረድቶ በአግባቡ የሚይዝና የዲሞክራሲን ባህል አዳብሮ ለተግባራዊነቱ የሚንቀሳቀስ አምራች ዜጋ እንዲሆን፡-

- የተጠቃሚውን (ወጣቶች፣ጎልማሶች ሴቶችና የልዩ ፍላጐት ትምህርት ያላቸውን ዜጎች) ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ትምህርታዊ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ፣ በተጠቃሚው ፍላጎትና ችግሮች ላይ የተመሠረቱ ፕሮግራሞችን መዘርጋት፣

- የጎልማሶች ትምህርት በመልካም የዜግነት እሴቶች የታነፀ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሀላፊነትን መወጣት የሚችል ለህዝብ ጥቅም የቆመ በሀቀኝነት በታማኝነትና በግልጽነት ሀሳቡን ማንሸራሸር የሚችል ብቁ ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል ይዘት በስርዓተ- ትምህርት ማካተት፣
- አግባብነት ያላቸው ባለድርሻ አካላትን (የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ አሠልጣኝ ተቋማት፣ የክልል-መንግሥታት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማሕበራትና የግሉን ሴክተር) በማሳተፍ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት መርህንና ቅደም ተከተልን መሠረት ያደረገ የመነሻ ሥርዓተ-ትምህርት ማዘጋጀት፤ ይህም፡-
    - ሙያ-ተኮር የጎልማሶች ትምህርት፣
    - በግል ሥራ ለመሠማራት የሚያስችሉ ፕሮግራሞች (ከክህሎት ሥልጠና ጋር የተያያዙ ወዘተ)፣
    - ለሥራ ፈጠራና ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ የሚሆኑ የሙያ ትምህርትና ሥልጠና፣
- የትምህርት መስጫ ማዕከላት ተለዋዋጭ ከሆነው አካባቢያዊና ሀገራዊ የምርትና የገበያ ሁኔታዎች ጋር ራስን ለማጣጣም እንዲቻል በመረጃ ማዕከልነት ያገለግላሉ፡፡
- በልዩ ሁኔታ ላሉ የማሕበረሰብ ክፍሎች የሚዘጋጁ ፕሮግራሞችን ያካትታል፡፡

- በተለያዩ አካባቢ ለሚኖሩና የተለያዩ ፍላጎቶች ላላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ተስማሚ የሆነ የመማርያ ማስተማርያ መፅሀፍትን ለማዘጋጀት የሚያግዝ የመነሻ ሥርዓተ-ትምህርት ማዘጋጀት፣

## 4.2.2. የጐልማሶች ትምህርት አመቻቾችን፣ ሱፐርቫይዘሮችንና ሌሎች ባለሙያዎችን የማስፈፀም አቅም መገንባት

ለትምህርት ጥራት ወሳኝ ከሆኑት ግብአቶች አንዱ የመምህራን በተገቢው ሁኔታ መገኘትና ብቃት ነው። እንደሚታወቀው ጎልማሶች በማሕበረሰቡ ውስጥ የራሳቸው ቦታ ያላቸውና የብዙ ተሞክሮዎች ባለቤት በመሆናቸው ጎልማሶችን ማስተማር የራሱ የሆኑ ዘዴዎች ይጠይቃል። የአመቻቾች ብቃት ለጎልማሶች ትምህርት አሰጣጥና ስኬታማነት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ስለሆነም ለተግባራዊነቱ፡-

- የጎልማሶች ትምህርትን በተሟላ ሁኔታ ለማካሄድ የፕሮግራም አመራሮችን፣የአሠልጣኝ ተቋማትን፣ አሠልጣኞችንና ባለሙያዎችን እንዲሁም አመቻች መምህራንን የማስፈፀም አቅም በበቂ ሁኔታ ማሳደግ፣
- ለጎልማሶች ትምህርት አመቻቾችን የሥልጠና ሥርዓት በመዘርጋት ሥልጠናውን በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ማካሄድ፣

- የጎልማሶች ትምህርት አመቻቾች ከአካባቢው ማሕበረሰብ የተመለመሉ፣ ቢያንስ የ10ኛ ክፍል ያጠናቀቁና በማሕበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።ይህ ሁኔታ በታዳጊ ክልሎች እንደአካባቢው ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
- የጎልማሶች ትምህርትና ሥልጠና የሚሠጡ የልዩ ልዩ የመምህራን ትምህርትና የግብርና ኤክስቴንሽን ማሠልጠኛ ኮሌጆች የሥራና የሥልጠና አቅም በጋራ በመፈተሽ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ስልጠና መስጠት፣
- በፌደራል፣ በክልልና በወረዳ ደረጃ በጎልማሶች ትምህርት ለተሰማሩ የተለያዩ ሱፐርቫይዘሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማካሄድ፣
- በዩኒቨርስቲዎችና በማሠልጠኛ ተቋማት ያሉ ባለሙያዎች በዘርፉ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለጎልማሶች ትምህርት መጠናከር አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና በተገቢው መንገድ ባለሙያዎችን በማሰልጠን ዘርፉን የሚያጠናክሩበትን ዘዴ መቀየስ፣
- ዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች የማሠልጠኛ ተቋማት የተዋጣለት የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞች እንዲያካሂዱ የበጀትና ሌሎች ድጋፎችን መስጠትና የውስጥ አደረጃጀታቸውን ማሟላት፣

### 4.2.3 የትምህርት መሣሪያዎችና ቁሳቁሶችን በማሟላት ምቹና ዘላቂነት ያለው የመማሪያ አካባቢ መፍጠር

የመማር፡ የማወቅና ግንዛቤ የማሳደግ ሂደት የበለጠ ውጤታማ የሚሆነው በሁሉም መስኮች ግብአቶችን አሟልቶ መጠቀም ሲቻል ነው። በመሆኑም የትምህርት መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች መሟላት የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም፤

- የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍትና አጋዥ የንባብ ጽሁፎችን ከጎልማሶች ኢለታዊ ኑሮ፣ ፍላጎትና ከአካባቢው ጋር በማገናዘብ በመርሀ-ትምህርቱ መነሻነት በክልሎች ይዘጋጃሉ፡፡
- የመማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ቁሳቁሶች በትምህርትነት የሚቀርቡ ይዘቶችንና ተግባራዊ ልምዶችን ያካተቱ ሆነው ጎልማሶች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ (በመስክ) ሊጠቀሙባቸው በሚችል መልኩ ይዘጋጃሉ።
- አዲስ አንባብያን የንባብና የጽህፈት ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበትን ሁኔታ በመለየት እንደፍላጎታቸው ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍትን በማዘጋጀት የማይምነትን ግርሻ መከላከልና የንባብ ባህልን ማዳበር፣
- የመንደር የንባብ ቤቶችን መፅሐፍት ማሟላት፣ የተጠቃሚውን የንባብ ባህል ማዳበር፣ በባህል ማዕከልነትና በመወያያ ስፍራነት እንዲያገለግሉ በማደራጀት የዲሞክራሲ ባህልን ማጠናከር፣

- በማሕበረሰቡ ውስጥ የጎልማሶች የመማር ሁኔታ እንዲቀጥል አስፈላጊ መማሪያዎች ቁሳቁሶችን መለየትና ማሟላት፣
- ተስማሚ የንባብ መማሪያዎችና ቁሳቁሶችን ዝግጅትና አቅርቦትን በማሳደግ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ቤቶችን የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላትና ሌሎች ለህብረተሰቡ አመቺ የሆኑ የመማሪያ ቦታዎችን በትምህርት መስጫ ማቢያነትና በንባብ ማዕከልነት መጠቀም፣
- ሕብረተሰቡ የመረጃና ግብብነት (የኮሙኒኬሽን) ቴክኖሎጂ በቅርብ የሚያገኝበትን ሁኔታ ለማሳደግ የጎልማሶች ትምህርት በሬዲዮና በICT የሚደገፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

## 4.2.4. ለውጤታማ የጎልማሶች ትምህርት የትምህርቱን አሰጣጥ ስልቶችንና ቴክኒኮችን ማሻሻል

- ለተለያዩ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞች ተስማሚ የሆኑ የትምህርት አሠጣጥ ዘዴዎችንና አቀራረቦችን በመለየት እንደአስፈላጊነታቸው ጥቅም ላይ ማዋል፣
- የጎልማሶች የመማር ሂደትን ጥራት ባለውና ውጤታማ በሆነ መንገድ ማመቻቸት ይቻል ዘንድ ለሥራ ሃላፊዎች፣ ለሱፐርቫይዘሮችና ለአመቻቾች ክህሎታቸውን የሚያዳብር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀት /መስጠት/፣

- በጎልማሶች ትምህርት አሠጣጥ ዘዴ ላይ የተመሠረተ የሥልጠና ማኑዋሎችን ማዘጋጀት፣
- የትምህርት ደረጃ ምደባና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት ማዕቀፍ እንደ አስፈላጊነቱ ማዘጋጀት፣

## 4.3. የጎልማሶች ትምህርትን ሽፋን በፍትሃዊነት ማሳደግ፤

- ለችግር ተጋላጭ የሆኑና መሠረተ ልማት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በልማት መርሀግብሮች በብቃትና በአቻነት ሰሜት እንዲሳተፉ ተግባር-ተኮር መሠረተ ትምህርትን ማስፋፋት፣
- ለገጠር አርሶአደሮችና በከተማ አነስተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ የሕብረሰብ ክፍሎች ተስማሚ የሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣
- ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ከተሰማሩበት የሥራና የኑሮ ሁኔታ ጋር የተጣጣሙ ፕሮግራሞችን መቀየስ፣
- ለሴቶች በተለይም ለድሀ ሴቶች ዕለታዊ ኑሮአቸውን ሊያግዙ የሚችሉና ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን መሠረት ያደረጉ ተግባር-ተኮር መሠረተ ትምህርት ፕሮግራም መዘርጋት፣
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ተስማሚ የሆኑ የመማርያ ቦታዎችና የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎችን ማመቻቸትና መተግበር፣

- በተለይዩ የኑሮ ሁኔታ ለሚኖሩ የአርብቶ አደር ሕብረተሰብና ልዩ ፍላጎት ላላቸው አካል ጉዳተኛ ሴቶች ተስማሚ የሆኑ የትምህርት ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ልዩ ትኩረት መስጠትና ተሣትፎአቸውን ማሳደግ፡

## 4.4. የጎልማሶች ትምህርት በተከታታይ የሚሰጥበት ተቋማዊ ሥርዓት መዘርጋትና አቅም መፍጠር

### 4.4.1 የጎልማሶች ትምህርት አመራርና አደረጃጀት

የጎልማሶች ትምህርት በተጠቃሚው ፍላጎት ላይ የሚመሰረትና ዘርፈ ብዙ ክንዋኔዎችን የሚጠይቅ ነው ።ጎልማሶች መማር የሚፈልጉት ከዕለት ኑሯቸው ጋር የተገናኘ፣ ችግሮቻቸውን ሊቀርፍ የሚችልና በኑሯቸው ለውጥ የሚያመጣ ሆኖ ሲያገኙት ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ባለፉት ዓመታት የተካሄዱት የጎልማሶች ትምህርት ኘሮግራሞች ወጥነት የጎደላቸውና ያልተቀናጁ በመሆናቸው የሚጠበቀውን ውጤት አላስገኙም። እነዚህ ውስን የልማት ጥረቶች በተጠቃሚው ዘንድ ሥርፀት እንዲያገኙና ዘላቂነት እንዲኖራቸው የተጠናከረና የተቀናጀ አመራር አደረጃጀት ኖሮት ሊካሄድ ነው። ስለዚህ፡-

- ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማለትም የግብርናና ገጠር ልማት፣ የጤና ጥበቃ፣ የሴቶች ጉዳይ፣ የወጣቶችና ስፖርት፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ሌሎች አካላትን እንደአስፈላጊነቱ በማስተባበር የተቀናጀ አመራር መስጠት

አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓቱን መሠረት በማድረግ በየደረጃው የጎልማሶች ትምህርትን በተጠናከረና በተቀናጀ ሁኔታ ማደራጀት፣

- ባልተማከለው የመንግሥት አደረጃጀት መሠረት የጎልማሶች ትምህርትን ለማስፋፋት የፌዴራልና የክልሎችን ሚና መወሰን፣ የተለያዩ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን ለማጠናከርና አስፈላጊ ድጋፎችን ለመስጠት ተጨባጭ እቅዶች በየደረጃው ይዘጋጃሉ።
- በክልሎችና ወረዳዎች አደረጃጀቱ ከላይ የተጠቀሱትን የልማት መስሪያቤቶችን ያካተተ ሆኖ በክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ የጎልማሶች ትምህርትን የሚመራ አካል ይቋቋማል።
- በትምህርት ዘርፉ በፌደራል፣ በክልልና ወረዳ የጎልማሶች ትምህርትን የሚያስተባብር አካል በየደረጃው ተጠናክሮ ይደራጃል።

## 4.4.2. ዘላቂና ውጤታማ የግንኙነት መረብ መዘርጋትና አጋርነትን መፍጠር

- በጎልማሶች ትምህርት ዘርፍ የተሠማሩ መንግስታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ኤጀንሲዎችን እንዲሁም ወደፊት በዘርፉ ለመሰማራት አቅሙና ፍላጎቱ ያላቸውን መለየትና በየደረጃው አጋርነትን ማጠናከር፣
- በጎልማሶች ትምህርት የተለያዩ ተግባራትን በተመለከተ ማን ምን ሊያከናውን እንደሚችል ለመወሰን የምክክር አውደጥናቶችን ማካሄድ፣

- በጎልማሶች ትምህርት የሚከናወኑ ተግባራትን ለማከፋፈል፣ በጋራ ለማከናወንና በአሠራር ቅደም ተከተል ዝግጅት የጋራ ግንዛቤ ላይ ለመድረስ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀትና እንደአስፈላጊነቱ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም፣
- በተቻለ መጠን አሁን ያለውን የግንኙነት መረብ በመጠቀም በየጊዜው ሀሳቦችንና ተሞክሮዎችን ለመጋራት በጋራ ለማቀድና አሠራሮችን ለመፈተሽ የሚያስችል የውይይት ፎረም ማቋቋም፣
- በጎልማሶች ትምህርት የሚከናወኑ ተግባራትን በጋራ ለማከናወን፣ በአሠራር ቅደም ተከተል ዝግጅት ላይ ለመመካከር፣ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፣ የተለያዩ ተግባራትን በተመለከተ ማን ምን ሊያከናውን እንደሚችልና በመተጋገዝ መሥራት ስለሚቻልበት ሁኔታ በጋራ ስልት መቀየስ፣

## 4 .4.3. ውጤታማ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት

- የጎልማሶችን ትምህርት ለመከታተልና ለመገምገም የትምህርት ሚኒስቴርንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን አቅም ማጠናከር፣
- የመረጃ ሥርዓት አመራር ማቋቋም፣
- አሳታፊ የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት፣

- ከባለድርሻ አካላትና አጋሮች ጋር በመሆን የፕሮግራሙን አፈጻጸም በየጊዜው መከታተልና መገምገም፣
- የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶች በወቅቱ ለባለድርሻ አካላት መሠራጨታቸውን ማረጋገጥ፣
- የክትትልና ግምገማ ሂደቶች የጎልማሶች ትምህርት መርሆዎችን መሠረት አድርገው መከናወናቸውን ማረጋገጥ